# ወንድ ይውጣህ!
# ሕዝብ መሃከል ገብተህ እፍ እፍ እያልህ
# ግብታዊ አመጽ አንድድ

***ከአስተዋይ በቀለ***

*ይገርማል! ዘንድሮ ነፃነት ለአህዮች ሆኖ በእነርሱ ልጓምና አለንጋ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ተለጉሞና ታፍኖ እየተገረፈ ነው። ምን ይደረግ! የወያኔ ፖለቲካ በረዶ በበጋ፣ ዝናብ በመከር ሆኗል።*

*አእምሮ የጐደለው ነገር ግን ምላሱን ያጣፈጠ ተቃውሞ ደግሞ፣ ሕዝቡን ሽንፈት ላይ ጥሎ፣ ወያኔን አስደስቶ ዘሎ ጉድጓድ ገብቷል። ጉድጓድ ውስጥ ተቀርቅሮ መውጫ ላጣው ተቃውሞ ይብላኝ እንጂ፣ እኛስ መተማመኛችን ምንጊዜም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።*

*ሕዝብ ያመነ፣ ሕዝብን መሠረት ያደረገ ሕዝብን ያቀፈ፣ የሕዝብን ቁጣ የሚያነድና አብሮ በግብታዊነት የሚያምጽ ምንጊዜም ድልን ይቀናጃል። ምክንያቱም ቁልጭ ያለ ሃቅ ነው። የማንኛውም ፀረ- መንግሥት ትግል መሠረቱ፣ ወሳኙና ታሪክ ሰሪው ኃይል ምንጊዜም ሕዝብ ነው።*

*ሕዝብ በግብታዊነት ከተነሣ እንደ እባብ ይነድፋል እንደ እፉኝትም መርዙን ነስንሶ ኢላማውን በመደምሰስ ሥር ነቀል ለውጥ ያመጣል። ለዚህ ሰሞኑን ቱኒሲያ ውስጥ የታየው ክስተት ትኩስ ማስረጃ ነው።*

*ጉሊት ላይ ተወዝፎ ይሸጥ በነበረ በአንድ ተጣጣሪ ድሃ ሰው የተቀሰቀሰው ግብታዊ እንቅስቃሴ፣ ቁጣውን በመንግሥት ላይ አንድዶ እንደ አልቀት ተጣብቆ ለረጅም ዘመን ደም ይመጥ የነበረውን መሪ በደረቅ ሌሊት አገር ለቆ እንዲወጣ በማድረግ መንግሥቱ ተነቅሎ ወድቋል።*

*ቀደም ብሎ ለምሳሌ የኬንያው ኪባኪ ተቃዋሚውን ፓርቲ እንዲያቅፍና አብሮ እንዲሰራ ያስገደደው ደረቱን ለጥይት የሰጠው የኬኒያ ሕዝብ ግብታዊ አመጽ ነው።*

*ነፍሳቸውን ይማርና አፄ ኃይለሥላሴን ከማይገሰሰው ስልጣናቸውና ከሰለሞናዊ ዙፋናቸው አሽቀንጥሮ የጣላቸው የ66ቱ የሕዝብ ግብታዊ አመጽ ነው።*

*ዛሬም እንደ ትላንቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በግብታዊነት ሊነሳና ለያምፅ የሚያስችለው በሳል ሁኔታዎችና የተካበተ ብሶት አለው። በአልታወቀ ጊዜና ሰዓት ትንሽ ነገር እንደሚጭረው አትጠራጠሩ። ያኔ ወያኔና ተለጣፊ ነቀዞችን ሳይነቅልና አሽቀንጥሮ ሳይጥል አይበርድም። አንተ የዚህ እንቅስቃሴ ቆስቋሽና እፍ እፍ እያልክ ቁጣውን የማንደድ ፍላጎት ካለህ ሕዝቡ መሃከል ገብተህ ተሰማራ። ወንድ ይውጣህ !!*